# በእነ አብይ ፣ቀይ ሽብር

ምርኮኛው ወታደር ፣ የዛሬው ጄኔራል
ባልተሟሸ አንደበት ፣ ህዝብ ላይ ያቅራራል
በአብይ አህመድ ፣ በለማ መገርሳ
የታጠቀው ገዳይ ፣ የዘውጌ ጨንባሳ
ባልተገራ ምላስ ፣ ቅርሻት ስላገሳ
አፍንጫ አይያዝም ፣ አህያ በፈሳ ።

የሸንፍላ መንጋ ፣ ታጥቦም የማይጠራ
የማያውቅበትን ፣ እየተንጠራራ
ትንንሽ ጭንቅላት ፣ አገር እየመራ
አላባራ ብሏል ፣ የዜጎች መከራ ።

ወንጌል ተሸክሞ ፣ እንደ ኢዩ ጩፋ
እንደ እስራኤ ዳንሳ ፣ ሽርክት ቁሪናፋ
ያጎረሰውን እጅ ፣ መልሶ የሚነክስ
አስመስሎ አዳሪ ፣ ገሎ የሚያለቅስ
ያከበረውን ህዝብ ፣ አፉን አሞጥሙጦ
ሲራገም ያመሻል ፣ ፓርላማ ተቀምጦ ።

በቁሮ የሚመራ ፣ በመጋ ዱርዬ
አገር እገዛለሁ ፣ የሚለው ሸንግዬ
የበሸሻው ቄሮ ፣ የሀሳብ ድንክዬ
የአዴፓው መሪ ፣ የአነግ ንቅሳት
አጭረህ አጭረህ ፣ ያመጣሃት እሳት
አዙረህ ወዳንተ ፣ ቂጥህ ስትለኩሳት
ያኔ ይገባሃል ፣ የሰራሃት ጥፋት ።

የአብይ ጄኔራል ፣ ከዕውቀት የተፋታ
በሃሳብ ሞግቶ ፣ ተከራክሮ አይረታ
ያሻንጉሊት መንጋ ፣ ልጓሙ የተፈታ
አፈሙዝ ወደ ህዝብ ፣ አለን ያለ ይሉኝታ
ዝንጀሮም አሳቃት ፣ መቦትረፉን ሰምታ ።

በሃሳብ ልዕልና ፣ አንሶ የታወረ
ከዕውቀት የተፋታ ፣ በዘውግ የሰከረ
መሸነፉን አምኖ ፣ ፍልሚያ እንደጀመረ
ደም የጠማው አውሬ ፣ ባፉ መሰከረ ።

ህዝብ ላይ የፈታው ፣ የቀወሰው ውሻ
ለሃጩ ጠብ እስኪል ፣ ቋምጧል ለንክሻ
ትዕቢት የነፋቸው ፣ ቅቤውና ሱሴ
የግንጠላ አበጋዝ ፣ የዘውግ እንደራሴ
ተናካሽ ውሻቸው ፣ በሰበቀው በትር
አገር ሊደማ ነው ፣ በእነ አብይ ፣ ቀይ ሽብር ።

ታዛቢው

July 13, 2019